ስለሆነ፣ በተረጋጋና በተለሳለሰ አካሄድ እንድትሄድ በማለት አላህ ማዕበሉን ትዕዛዝ አስኪሰጥ ደረስ ሳጥኑን ምንም ወታ አልነካውም ነበር። ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ አሳቱን ለኢብራሂም (ዐ.ሰ) ቀዝቃዛና ሰላማዊ እንዲሆን አንዳዘዘው ሁሉ ናይል ወንዝንም ይህን ሳጥን ፌርዓውን ቤተ-መንግሥት አስኪደርስ ድረስ ሙሳን በእርጋታ እና በዝግታ አንዲወሰደው አዘዘው። ውታውም ይህንን ውድ ሣጥን ወደ ፌርዓውን ቤተ-መንግሥት ወሰደው፣ ማዕበሉም ሣጥኑን ወደ ባሕሩ ዳርቻ ወሰደው። የዚያን ዕለት ንጋት ላይ የፌርዓውን ባለቤት በቤተ-መንግሥቱ ዙሪያ ባለው የአትክልት ስፍራ ስትዘዋወር ነበር፡ አገልጋይ ሠራተኞቿም ማሰሮአቸውን (ቶፋቸውን) ይዘው ውታ ለመቅዳት በሄዱበት ጊዜ ይህን ውድ ሣጣን አገኙት፤ ሣጥኑን ሳይከፍቱ ወደ ፌርዓውን ሚስት ተሸከመው ወሰዱት፣ እሷም እንዲከፍቱት አዘዘቻቸው፣ ይህ ሣጥን ሲከፈትም ሙሳን በውስጡ አየቸው። በልቧም ፍቅር ተሰማት ከሣጥኑም አነሳችው፣ ሙሳም ርቦት ስለነበር ከእንቅልፉ ነቅቶ ማልቀስ ጀመረ፣ የፌርዓውን ባለቤትም ይህን ሕፃን ይዛ ወደ ፌርዓውን ቀረበች።

ፌርዓውንም ይህን ሕፃን ከየት እንዳመጣችው ጠየቃት? እሷም ስለ ሳጥኑ ታሪክ ነገረችው። ምሕረትን በማያውቀው ልቡ፡- ይህማ ከእስራኤል ልጆች አንዱ መሆን አለበት አለ፣ ታዲያ በዚህ ዓመት ከሚገደሉት ሕፃናት ስለሆነ መገደል የለበትም ትያለሽ ሲልይጠ ይጠይቃታል? አሲያ (የፌርዓውን ሚስት) ልጅ መውለድ እንደማትችል ባሏን በማስታወስ ሕፃኑን እንድታሳድገው እንዲፈቅድላት ጠየቀችው፣ እሱም ፈቀደላት። ሙሳም (ዐ.ሰ) በረሃቡ ምክንያት ወደ ለቀሰው ተመለሰ። ማጥባት የሚችሉ ሞግዚቶችን እንዲመጡ አዘዘች አንዲት ማጥባት የምትችል ሞግዚት ከቤተ-መንግሥት መጥታ ሙሳን ልታጠባው ወሰደችው፣ እርሱ ግን ከእርስዋ ጡት ሊጠባ አልፈቀደም፤ ከዚያም ሌላ ሞግዚት መጣች አሁንም አልፈቀደም፣ ሶስተኛዋም እስከ አስረኛዋ አጥቢ ሞግዚቶች መጡ፣ እርሱ ግን እያለቀሰ ከሁሉም ጡት መጥባት አልፈለገም።

የፊርዓውን ሚስት ግራ ተጋባች፣ ምን ማድረግ እንዳለባትም አላወቀችም። ነገር ግን ሙሳ እነዚህ አጥቢዎችን ሁሉ ባለመቀበሉ የምታዝነው እና የምታለቅሰው የፊርዓውን ሚስት ብቻ አይደለችም፣ የሙሳ እናትም ልጇን ወደ ናይል ወንዝ የወረወረችው እምብዛም ቀላል ሐዘን የሚባል አልነበረም። ልቧን አውጥታ ወደ ወንዙ እየወረወረች እንደሆነ ነበር የተሰማት፤ ሣጥኑም ጠፋ፤ በናይል ውኃ ውስጥም ወረ ጠፋ፤ ጨለማውም ነጋ፣ ንጋት ላይ የሙሳ እናት ልቧ ባዶ ሆነ፤ በልጇም ላይ ሐዘንዋ በረታ። የልጇን ሁኔታ ለማሳወቅ ወደ ፊርዓውን ቤተ-መንግሥት ለመሄድ ወስና ነበር ማለትም ይቻላል።

ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ ልቧን ቢያጸናት፣ ነፍሷንም በሰላም ቢሞላት ኖሮ በልጇ ጉዳይ ተረጋግታ የአላህን ትዕዛዝ ትጠባበቅ ነበር፣ ነገር ግን እናት ናት እና ዝም ብሎ መቀመጥ አልተቻላትም፤ እናም የሙሳን እህት በቀስታ ወደ ከተማው ሂጂና የወንድምሽን ሙሳን ሁኔታ ለማጣራት ሞከሪ በማለት ላከቻት። የሙሳ እህትም በእርጋታና በቀስታ ወደ ፊርዓውን ቤተ-መንግሥት አጠገብ ሄደች፤ ከዚያም ታሪኩን ከዚህም ከዚያም መስማት ጀመረች፤ ከእሩቅ ስትከታተል የሙሳን ድምጽ ሲያለቅስ ሰማችው፣ ሰዎቹም ጡት አልጠባም በማለቱ ግራ ተጋብተው ምን ማድረግ እንዳለባቸው አላወቁም፤ ታዲያ ጡት መጥባትን እምቢ ማለቱን ሰምታ ለፊርዓውን ጠባቂዎች፣ ጡት የሚያጠቡትን ቤተሰብ ልምራችሁ፣ በደምብ ተንከባከበው ነው የሚይዙት፣ በሚግገባም የሚያሳድጉ ናቸው አለች፤ የፊርዓውን ሚስት በዚህ ነገር በጣም ተደሰተች እናም ያለቻትን ማጥባት የምትችል ሞግዚት እንድታመጣት ጠየቀቻት፣ የሙሳ እህትም ወደ ቤት ተመልሳ እናቱን ይዛት መጣች። እሷም ጡቷን አጥባ አጠባችው የፊርዓውን ሚስት በደስታ ተሞላች እና ለሙሳ እናት እንዲህ አለቻት፡- “እርሱን ወሰጂው እና ጡት በማጥባት አሳድጊው፤ ጡት የሚጠባበት ጊዜው ሲያበቃ ወደኛ መልሺው፤ ያሳደግሺበትንም ትልቅ ምንዳ እንከፍልሻለን።”

አያችሁ በጭንቅና በደስታ መካከል አንድ ቀንና ሌሊት ብቻ ነበር የነበረው። ነገሩ ሁሉ በእጁ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) ጥራት ይገባው እና ለሚፈሩት ሰዎች ከጭንቀት ሁሉ አፎይታን ከጭንቀትም ሁሉ መውጫን እና ማምለጫን ይሰጣል።

♦♦♦○♦♦♦

አካል ጉዳተኞች ተሰፋ መቁረጥን ተቃወሙ

- ሳዲቂ

ሙሉ የሰውነት አካሉ የሰለለ በመሆኑ ምክንያት የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የሚሰቃየው ኢራናዊ ሠዓሊ ሳዲቂ፣ አልጋው ላይ ተኝቶ የሥዕል ብሩሹን በእጆቹ መካከል በማድረግ ያስደመሙትን ነገሮች በነጩ ሸራ ላይ መሣል ጀመረ። ልክ የአሥራ ስድስት ዓመት ልጅ እያለሁ በደረሰብኝ የመኪና አደጋ ከአንገቴ በታች ሰባተኛው የአከርካሪ አጥንት ስብራት ከደረሰብኝ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ መላ ሰውነቴ በሚባል ደረጃ ከአንገቴ ጀምሮ ወደታች መንቀሳቀስ የማይችል ሆኛለሁ፤ ጣቶቼ ሳይቀሩ ነበር መሥራታቸውን ያቆሙት። ሥዕልን ለመለማመድ ከጓደኞቼ እና ከማውቃቸው ሰዎች በርከት ያሉ የማበረታቻ መልዕክቶችን አግኝቻለሁ፣ በዚህም ወደፊት ሠዓሊ ለመሆን አስቦ የማያውቀውን የግል ፍላጎቴን ምን ያክል ጥልቅ እንደሆነ ለማወቅ ችየበታለሁ። በሚደንቅ ሁኔታ ግን ከመኪና አደጋው በፊት የሥዕል ፍላጎት አልነበረኝም ነበር፣ ወደፊትም ሠዓሊ እሆናለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር።

- ኢብኑል ሙቅፈዕ

በመጻፍ ብዛት ጣቶቹ ደንዝዘው የተጎዱበት ይህ ልዩ ጸሐፊ በሕይወቱ ትግሉን እስከ ዕለተ ሞቱ የቀጠለው መጻፉን ሳያቆም ነበር። ይህ ጸሐፊ ካሊላ እና ደምና የተባሉ መጽሐፍቶችን ወደ ዓረብኛ የተረጎማቸው እሱ ነው። ደንዝዘው የተጎዱ ማለት፣ በሀመም እና በብርድ ምክንያት ጣቶቹ የተጎዱበት እንደማለት ነው፤

እነዚህን እጆቹን ታዲያ ከብርድ ለመከላከል ኪሶቹ ውስጥ ነበር አስገብቶ የሚንቀሳቀሰው!

- ስቴፈን ሃውኪንግ፡

እንግሊዛዊው የፊዚክስ ሊቅ እና ፕሮፌሰር፣ ምንም እንኳን ከልጅነቱ ጀምሮ ኳድሪፕሌጂያ በተባለ በሽታ እየተሰቃየ ቢኖርም በታሪክ ውስጥ ከታላላቅ የፊዚክስ ሊቃውንት አንዱ ተደርጎ ይወሰዳል።

- ባሻር ቢን በርድ

በጥንታዊው ዘመን ከአይታ አከል ጋር ተያይዘው ካሉት የፈጠራ ምሳሌዎች አንዱ ተደርጎ የሚወሰደው ዓይነ ስውር ገጣሚ።

- የተቆለፈበት (አቡልዓላእ አል-መዕሪ)

በጣም ታዋቂው አካል ጉዳተኛ ገጣሚ ራሱን የሁለቱ ማረሚያ ቤቶች (ዓይነ ስውርነት እና ማረሚያ ቤት) ታጋች ብሎ ጠርቷል፣ መጽሐፎቹም በአንዳንድ የአውሮፓ የግጥም ሥራዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ ነበሩ።

- አል-በርዱኒ

ዓይነ ስውሩ የየመን ባለቅኔ፤ እና ታዋቂ ከሆኑ የወቅቱ የዓረብ ገጣሚዎች አንዱ የነበረ ነው። በረጅም የፈጠራ ታሪክ እና ከሕይወት ጋር በመታገል የዘመኑ ገጣሚ ተብሎ መጠራት ደርሶ ነበር።

- ከላስ አሱወይዲ

የጄነቲከስ ወይም የሥነ-ዘረመል ባለሞያው፤ ዝላይ በሚለማመድበት ወቅት አከርካሪው ላይ በደረሰ ጉዳት አካል ጉዳተኛ ሆነ፤ ከዚያም ከሁለት ዓመት በኋላ ዘረመል በማዳቀል ሳይንሳዊ ድል አስመዝግቧል።

- ራያን ማርቲን

የአካል ጉዳተኛው ዶክተር፤ አካል ጉዳተኛ የቴኒስ ተጫዋች የነበር ሲሆን በዓለም 21ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጦም ያውቃል።

- ዶ/ር ጢሃ ሁሴን

ጢሃ ሁሴን እ.ኤ.አ በ1889 የተወለደ ሲሆን ገና በልጅነቱ በግብጽ ገጠራማ መንደር ኖረ ከዚያም ወደ አል-አዝሃር ሄዶ ትምህርቱን ለመማር ሞከረ፤ ነገር ግን አልተሳካለትምና ወደ ግብጽ ዩንቨርሲቲ ተዛወረ የመጀመሪያ የዩንቨርሲቲ ዲግሪውን አገኘ፤ ከዚያም ከስኮላርሺፕ ኮሚቴው ብዙ ተቃውሞ ቢያጋጥመውም፤ ፍላጎቱ በፓሪስ የድህረ ምረቃ ትምህርቱን እንዲጀምር ገፋፍቶታል። ነገር ግን ማመልከቻውን ሦስት ጊዜ ደጋግሞ በማስገባት በመጨረሻ በፓሪስ የዶክትሬት ዲግሪውን አገኘ። ወደ ግብጽ ከተመለሰ በኋላ በሕይወት ዙሪያ፤ በቀኖች ዙሪያ፤ እንዲሁም በግብጽ ባህል የወደፊት እጣ ፈንታ እና ሌሎችንም ጨምሮ ብዙ ጠቃሚ ሥራዎችን ሰርቷል።

♦♦♦○♦♦♦

አላህ... ለለጸጋማነቴ እለምንሃለሁ

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) - ከአላህ ዘንድ የወረደላቸውን ነገር ከርሱ ዘንድ እንደሚቀበሉ ተስፋ በማድረግ እና ከሠቂፍ ሕዝብ ድጋፍን ለመሻት ብሎም ከሕዝቡ ተንኮል ጥበቃ ለማግኘት ወደ ጣኢፍ አመሩ። ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ጢኢፍ

ሲደርሱ ወደ ሰቂፍ ጎሳዎችም ሄደው በዚያን ጊዜ የአካባቢው ሊቃውንት እና መኳንንት ወደነበሩት ሰዎች ጋር በመቀማመጥ፣ ለእስልምና ያላቸውን ድጋፍና የራሳቸው ሕዝብ እየተቃወሟቸው ስለሆነ ከጎናቸው እንዲቆሙ አግረመንገዳቸውንም አላህ ያወረደላቸውን ነገር በማስታወስ ወደ አላህ (ሱ.ወ) ጠሯቸው። ከመካከላቸውም አንዱ እንዲህ አላቸው፡- አንተ እንደምትለው የአላህ መልዕከተኛ ከሆንክ አንተን ማናገር ለኔ በጣም አደጋ ነው፤ እየዋሸህ ከሆነ ደግሞ ላናግርህ አይገባም አላቸው።

የአላህ መልዕከተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ከሠቂፎች መልካም ነገር አገኛለሁ በሚለው ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ከቦታው ተነሱ፤ ሰዎቹም በእርሳቸው ላይ እስኪሰበሰቡና እስኪጭሁባቸው ድረስ አገልጋዮቻቸውን እና ባሮቻቸውን ወደ እርሳቸው ላኩ። ከዚያም ወደ ዑትባህ ቢን ረቢዓህ እና ወደ ሸይባህ ቢን ረቢዓህ ቅጥር ግቢ ወሰዷቸው። እርሳቸውም ወደ ወይኑ የዘለላ ጥላ ሄደው አረፍ አሉ። ከተረጋጉም በኋላ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡

አላህዬ ደካማነቴን፣ ብልሀት የሌለኝ መሆኔን እና ከሰዎች ዘንድ ደካማ ስለሆንኩ አቤቱታዬን የዓለማቱ አዛኝ ወደሆንከው ወዳንተ ነው ማቀርበው፤ አንተ የደካሞች ጌታ ነህ፤ የኔም ጌታዬ ነህ፣ ለማን አደራ ሰጠኸኝ?። እኔንስ እስከ መቼ ነው የምትረሳኝ? ጉዳዬን ለማን ተውከው? በእኔ ላይ ካልተናደድክብኝ ምንም ግድ የለኝም፣ ነገር ግን ደህና ከዋልክልኝ ለእኔ በላጩ አሱ ነው። ቁጣህ ከሚወርድብኝ ደግሞ ጨለማውን በገፈፈው የፊትህ ብርሃን እንዲሁም የቅርቢቱን እና የሩቋን ዓለም ባስተካከልክልኝ አንተነትህ እጠበቃለሁ፣ ወይም ደግሞ ቁጣህ በእኔ ላይ እንዳይደርስብኝ እስክትወድልኝ ድረስ እለምንሃለሁ፤ ብልሃትም ሆነ ኃይል ከአንተ በቀር የለም።

የረቢዓን ልጆች ዑትባንና ሸይባን እንዲሁም የተገናኟቸውን ባየ ጊዜ ርኅራኄያቸው አደረባቸው እና ከሙሽሪኮች የሆነውን ዓዳስ የተባለውን ልጅ ጠርቶ፡ ከእነዚህ ወይኖች ወስደህ በዚህ ሳህን ላይ አስቀምጥ እና ወደዚያ ሰው ወስደህ ከፍሬዎቹ

አንዲበላ ንገረው አለ። ዓዳስም አንደታዘዘው አደረገ እና መልዕከተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እጅ ላይ ካስቀመጠው በኋላ፡ በል ብላ አላቸው፤ አሳቸውም ቢስሚላህ (በአላህ ስም) በማለት በሉ። ዓዳስ ቀና ብሎ በመመልከት በአላህ አምላለሁ ይህንን ንግግር የዚህች አገር ሰዎች የሚሉት አይደለም አለ።

ከዚያም የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ) "አንተ ዓዳስ ሆይ ከየትኛው አገር ሰዎች ነህ ኃይማኖትህስ ምንድን ነው?" አሉት። እርሱም፡ እኔ ከርስቲያን ነኝ፤ የነይነዌ ሰዎች ሰውም ነኝ አለ። ከዚያም የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ) "ከመልካሙ ሰው ዩኑስ ቢን መታ መንደር ማለት ነው አሉት?" ዓዳስም፡ ዩኑስ ቢን መታ ምን እንደሆነ በምን አወቅከ? አላቸው የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፡ "ወንድሜ ነው፤ አሱ ነብይ ነበር አኔም ነብይ ነኝ" አሉት።

ከዚያም ዓዳስ የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ደገፍ ብሎ ግንባራቸውን፤ እጃቸውን እና ጉልበታቸውን እየሳመ በተመለከቱ ጊዜ፤ ከሁለቱ የረቢዓህ ልጆች መካከል አንዱ ለጓደኛው እንዲህ አለው፡ ልጅህን አበላሽቶታል በማለት... ዓዳስ ወደ አነርሱ በመጣ ጊዜ፤ ወዮልህ ዓዳስ፤ የዚህን ሰው ግንባር፤ እጁና እግሩን ለምንድን ነው የሳምከው? አሉት? እንዲህም አለ፡ ጌታ (አሳዳሪዬ) ሆይ በምድር ላይ ከዚህ የተሻለ ነገር የለም፤ ነብይ ብቻ የሚያውቀውን ነገር ነው የነገረኝ።

እኚህ ተወዳጅ ነብይ የጢኢፍ ቀንን ከከባድ ጭንቀት ጋር የተጋፈጡበት እና ከባድ ከሆኑት ከሠቂፍ ጎሳዎች ጋር በመገናኘታቸው ተወዳጅ ያደርጋቸዋል፤ ይህች ቀን ጎሳዎች ጥሪ በሚያደርጉበት ወቅት ካጋጠሟቸው ሁሉ የበለጠ ከባድ ቀን አድርገው እንዲያስታውሷቸው አድርጓቸዋል። በእርሱ ሰበብም አላህ የከሰራን እና ቁይሳርን ሀብት ከፈተላቸው፤ ኃይማኖታቸውንም ከምሥራቅ እስከ ከምዕራብ አሰፋፋ።

የነብያችን ኃይማኖት (ዲናቸው) ከርሳቸው በፊት የነበሩትን ኃይማኖቶች የሻረ ሆነ...እንግዲህ አንባቢ ሆይ በእውነት የበላይ እና ፍፁም በረከት የተላበሱትን

የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ተመልከተህ (ፊዳከ - "አባቴም እናቴም ላንቱ ይሰውልዎት የአላህ መልዕከተኛ ሆይ") በል።

♦♦♦◯♦♦♦

አሳሹ መርከበኛ

ያሕያ አነሕዊ ተሳፋሪዎችን ከአንዱ አጥናፍ ወደ ሌላኛው በመርከብ እየወሰደ የሚኖር አሳሽ ነበር፤ ይህ ሰው ዕውቀትን በጣም ይወድ ነበር። በአሌክሳንድሪያ ደሴት በሚጓዝበት ወቅት የዕውቀት ባለቤቶች አብረውት ሲሻገሩ ሲያገኝ፤ ከዚህ በፊት ስለነበራቸው ትምህርት መወያየትና መደራደር ይጀምራል፣ ለዕውቀትም በጣም ይጓጓ ስለነበር ቃላቶቻቸውንም በጥሞና ነበር የሚያዳምጠው። ዕውቀትን በመፈለግ ዙሪያ ያለውን አስተያየት አጠናክሮ ቀጠለ። ራሱንም እንዲህ ሲል ጠየቀ፡ ዕድሜዬም ከአርባ ዓመት በላይ ሆነ፣ ነገር ግን ከአሰሳ እና ከባሕር ኑሮ ውጭ ምንም ነገር ስለማላውቅ በሕይወቴ ደስተኛ አይደለሁም፤ እና ታዲያ ካለሁበት ውጭ ስላለው ሳይንስ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

በተመለጦ ወስጥ እያለ አንዲት ጉንዳን የተምር ፍሬን ተሸክማ ለመውጣት ስትሞክር አየ፣ ከዚያም ፍሬው ወደቀባት፣ ተመልሳ ወረደች እና ወሰደችው፣ የትግል ግቢን አስክትመታ ድረስ ደጋግማ ትግሏን ቀጠለች።

ያሕያ እንዲህም አለ፡- ይህች ደካማ ፍጡር በትግልና በመደጋገፍ ግቢን ካሳካች እኔስ በትግልና በመደጋገፍ ግቤን ባሳካ አይሻልም? በማለት ራሱን ጠየቀ።

ጊዜውን አሳልፎ መርከቢን ሸጦ ወደ ዕውቀት ቤት ሄዶ ሰዋሰው፣ ቋንቋንና ሎጂክን ይማር ጀመር። በእነዚህም የትምህርት ዘርፎች ራሱን ለላቀ ደረጃ አደረሰ፣ ምክንያቱም መጀመሪያ ያስጀመራቸው እርሱ ነበርና፣ ለሌሎችም ተረፈ፣ በመጨርሻም በዚሁ የትምህርት ዘርፍ ታዋቂ ሰው ሆነ።

♦♦♦◯♦♦♦